# <u>የመጨረሻው ደወል</u> !

(አሥራደው ከፈረንሳይ)



ኳ! ኳ! ኳ!  ይላል፤
በማርያም ደጃፍ - በገብርኤል፤
በጎርጊስ ደጅ - በሩፋኤል፤
በጨርቆስ ደጃፍ - በአማኑኤል፤
በተክልዬ - በሚካኤል፤

ኳ!  ኳ!  ኳ!  እያለ፤
የመጨረሻው ደወል ተደወለ፤
አትንበርከክ በቃ !
ቆመህ የጴጥሮስን ሞት ሙት አለ።

ስደት አገር አሟጦ - ሃዘን ሰብዕናህን አጉብጦ ፤
ችጋር አጥንትህን ግጦ - ፍርሃት አንቀጥቅጦ ፤
ድህነት አፍጥጦ - በደል አንፈራጦ ፤
አይግዛህ ይበቃል !
የአያት የቅድም አያቶችህ ቃል፤
እንቢኝ ነው ደጉ - እንቢኝ ይበልጣል።

ይዩት  ድፍረትህን !
ይወቁት ኩራትህን !
አትበርከክ  ይበቃል፤
እንቢኝ በል ! - እምቢኝ ይሻላል።

የልጆችህ አንገት_ በጠራራ ፀሐይ ሲቀጭ ፤
የአያት የቅድም አያቶችህ_ አጽም ሲንቀጫቀጭ ፤
ተንበርክከህ ሳይሆን_ አጎንብሰህ ፤
የጀግኖችን ሞት ሙት_ ቆመህ !
የአያት የቅድም አያቶችህ ወጉ ፤
እምቢኝ ይሻላል_ አሻፈረኝ! ነው ደጉ ።

ሞት በገዛ እጁ አፈረ !
ክርስቲያንና እስላሙ_ ተባበረ፤
በኢትዮጵያ ምድር - አብሮ እንደኖረ፤
በአንድነት ቆሞ - መሞት ጀመረ ።

አትፍረከረኪ_ ጽና በዕምነት !
የጀግና ልጅ ጀግና_ መሆንክን ይወቁት፤
ለጨቋኞች አትንበርከኪ_ ቁም ለነፃነት፤
ቆመህ ተጎንጫት - የጴጥሮስን_ ሞት

የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬም እንደ ጥንቱ፤
ማ'ተቡን አጸና በደምና_ ባጥንቱ ።

እነሆ ኳ! ኳ! ኳ! ይላል፤
የመጨረሻው ደወል ተደውሏል፤
የበደል ፍጻሜው_ ይሆናል ።

አንድ ቀን !

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !!

ነፃነት፤ እኩልነትና ወንድሟሟችነት ይለምልም !!

እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና ህዝቧን ይባርክ !!